# የወጅራት ባህላዊ የፍትህ አስተዳደር

**ጥናቱን ያከናወኑ ባለሙያዎች፡-**

ይድነቃቸው ከበደ

ኢሳያስ አየለ

ገ/መስቀል ገ/ዋህድ

## በጥናቱ የቀረበ ምክረ ሀሳብ

1. የወጀራት ባህላዊ ህግ ብዙ ጠቃሚ ህጎች እና አሰራሮች መኖሩ እውቅና ተሰጥቶት በመንግስታዊም ሆነ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ባህሉ እንዲያንሰራራ የሚደረግበትን ሁኔታ እና መፍትሄ መሻት አለባቸው፡፡
2. በአሁኑ ሰአት በተግባር እየተተገበሩ የሚገኙትን እንደ ገረብ አይነት አጎራባች ህዝቦች ጋር በሰላም ለመኖር፣ ግጭቶች እና አለመግባባቶች ሲነሱ አለመግባባቶችን መፍቻ መንገዶች በአግባቡ ተይዘው በተጠናከረ ሁኔታ የሚቀጥሉበትን ሁኔታ ቢመቻች
3. ጥልቅ እና ሰፊ ምርምሮች ቢደረጉ በበለጠ ባህሉን ለማሳደግ እና ለማጠናከር ይረዳል
4. ህግ አውጪውም ሆነ ፖሊሲ አርቃቂዎች ይህንን አኩሪ ባህል የሚያበረክተውን ጥቅም እና አስተዋጽኦ ከግምት በማስገባት ህጎች እና ፖሊሲዎች በሚወጡበት ወቅት ቢያጠኑት ጥሩ ይሆናል፡፡
5. ከወጪ ፣ፍትህን ተደራሽ ከማድረግ እንዲሁም ግጭቶች ለዘለቄታው ከመፍታት አኳያ በአካቢው የሚነሱት አለመግባባቶች እና ግጭቶች በአካባቢው ባህልና ልምድ እንዲፈቱ ቢደረግ የተሻለ ማህበራዊ ሰላም፣ ደህንነት እና ብልጽግና የሚሰጥ ይሆናል፡፡
6. አዲሱ ትውልድ ስለባህላዊ ህግ ያለው እውቀት አነስተኛ ስለሆነ ግንዛቤ ማስጨበጫ መድረኮች እና ማህበረሰባዊ ውይይቶች በሚመለከታቸው አካላት ቢዘጋጅና ቢጎለብት፡፡